# ኢትዮጵያ በውጭው ሚዲያ

ታከለ አለሙ 08-28-17

የተለያዩ አለምአቀፍ ሚዲያዎች ሀገራችንን በተመለከተ ሰፋፊ ዘገባዎችን በማቅረብ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሀገሪትዋ ሰፊ ትኩረት የመሳብዋ፤ ኢኮኖሚዋ በፈጣን ሁኔታ ማደጉ፣ የተፈጥሮ ሀብቷን በከፍተኛ ሁኔታ በመጠቀም ላይ መሆኗ ወዘተ በነዚህ ሚዲያዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እየተዘገቡ፤ እየተተነተኑ የሚገኙ ርእስ ጉዳዮች ናቸው።

ኢትዮጵያ አሕጉራችንም ሆነ አለም በሚጠብቀው መልኩ በልማትና በኢኮኖሚ እድገት እንዲሁም በዲፕሎማሲው መስክ ተሰሚና ተደማጭ ሀገር እየሆነች መጥታለች፡፡ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ባለፉት 25 አመታት ዘርፈ ብዙና ታላላቅ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከነዚህ ስራዎች መካከልም ለማሳያ ያህል የተወሰኑትን እንመለከታለን።

በጤናው መስክ ከጤና ጣቢያ እስከ ከፍተኛ ክሊኒኮችና ሆስፒታሎች፤ በትምህርቱ መስክ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ በርካታ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎችን የመገንባትና ማስፋፋት፤ አለምአቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ መንገዶችን፤ ዘመናዊ የመኖሪያ ቤቶች (ኮንዶሚኒየም) ግንባታዎችን፤ ዘመናዊ የአየር መንገድ የመገንባትና የማስፋፋት፤ በክልሎች ዘመናዊ ከተሞችን የማሳደግና መስፋፋት፤ የተለያዩና ግዙፍ የኃይል ማመንጫ ግድቦችን የመገንባት፣ የግብርናውን ዘርፈ በማዘመን ምርትና ምርታማነትን የማሻሻልና ማሳደግ፤ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች የማስፋፋትና የመሳሰሉ ስራዎች በስፋት ተሰርተዋል፡፡ ከላይ የጠቀስናቸው የመገናኛ ብዙሀን አውታሮች በርብርብ እየተናገሩትና እየሰጡት ላለው ምስክርነትም መነሻዎቻቸውና መረጃዎቻቸው እነዚሁ ኢትዮጵያ ያከናወነቻቸው ተግባራትና የተገኙት ስኬቶች ናቸው። በዲፕሎማሲውም መስክ ያለው ገፅታ ተመሳሳይ ነው።

በቅርቡ ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ በሱዳን በነበራቸው ቆይታ ከሀገሪቱ ፕሬዚደንት ኦማር አልበሽርና ከሀገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር መምከራቸውን *ሱዳን ትሪቡን* የተባለው ድረገጽና ሌሎችም ዘግበዋል፡፡ የሁለቱ መሪዎች ዋነኛ የመነጋገሪያ አጀንዳ በደቡብ ሱዳን ያለው የእርስ በርስ ጦርነትና የኢትዮጵያ የታላቁ የሕዳሴ ግድብ መሆኑን የሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኢብራሂም ጋንዱር ማስታወቃቸውን የዘገቡ ሲሆን፤ አቶ ኃ/ማርያም በሱዳን ቆይታቸው በሱባ ግዛት የሚገኘውን *የባሻ መድኃኒት ፋብሪካን* እንዲሁም በእንስሳት እርባታና በእርሻ ምርት ታዋቂ የሆነውን *ዳልፋርማስ* የእርሻ ቦታ መጎብኘታቸውንም አስነብበዋል፡፡

ሱዳን ትሪቡን ድረገጽ የሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት ኢብራሂም ጋንዱር የኢትዮጵያና የሱዳን ግንኙነት ምሳሌ ሊሆን እንደሚችል መግለጻቸውን ዘግቧል፡፡ የታላቁ የሕዳሴ ግድብን በተመለከተ ውይይቱ ግብጽን ባሳተፈ መልኩ እንደሚካሄድ፤ ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ግንኙነት ከውኃ ጉዳዮች ያለፈ መሆኑን፤ ውኃ የሱዳን፣ የኢትዮጵያና የሌሎችም የአባይ ተፋሰስ ሀገራት የብሔራዊ ደሕንነት ጉዳይ ነው ሲሊ መግለጻቸውንም ድረገጹ አስነብቧል፡፡

የሱዳኑ ፕሬዚደንት ኦማር አልበሽር ከኢትዮጵያ ጋር የድንበር ውዝግብ አለመኖሩን ማስታወቃቸውን ድረገጹ በሌላ ዘገባው አስታውቋል፡፡ የድንበር ማካለሉን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም አይነት ችግር እንደሌለው ፕሬዚደንቱ መናገራቸውን ድረገጹ ዘግቦ በድንበር ማካለሉ ላይ ሙሉ ስምምነት መኖሩን፤ በመደራደሪያ ነጥቦቹ ላይም ምንም አይነት አለመግባባት

አለመከሰቱን የጠቀሱት ፕረዘዳንቱ፤ የቀረው ነገር የድንበር መለያዎችን ማስቀመጥ ነው ሲሉ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ጋር በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ መናገራቸውን ድረገጹ አስፍሮአል፡፡ የሀገራቱ ሁሉን አቀፍ ትብብር ወደ ላቀ ደረጃ ለመድረሱ የጉብኝቱ ግብዣ ማሳያ መሆኑን የኢትዮጵያ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ሚኒስትር ዶ/ር ነገሪ ሌንጮ መግለጻቸውን ዘገባው ያስረዳል፡፡

የቻይናው ዜና ወኪል ሺንዋ በበኩሉ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በሱዳን ጉብኝታቸው ወቅት ኢትዮጵያ 50 በመቶ የሚሆነውን የወጪ ምርቷን በፖርት ሱዳን በኩል ለውጪ ገበያ የማቅረብ ፍላጎት እንዳላት ማስታወቃቸውን ዘግቧል፡፡

አፍሪካን ኒውስ ድረገጽ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በሱዳን ጉብኝታቸው ወቅት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ባሉ ሀገሮች ውስጥ ዘወትር ለሚስተዋለው የሰላም እጦትና አለመረጋጋት ችግር ዋነኛው ምክንያት ድሕነት መሆኑን መግለጻቸውን ዘግቧል፡፡ በአፍሪካ ቀንድ ሀገሮች ውስጥ ለዘመናት የሰፈነው ድሕነት፣ ድርቅ፣ ረኃብ እና በሽታ የበይነ ቀጠናውን ሀገሮችና ሕዝቦች ለእርስ በእርስ ግጭቶችና ጦርነቶች እንደዳረጋቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል ሲል ድረገጹ አስነብቦአል፡፡

የቻይናው ዜና ወኪል ሺንዋ ኢትዮጵያ በ2009 በጀት ዓመት ከለጋሽ ሀገራትና ከአጋሮቿ 3.4ቢለዮን ዶላር በብድርና በድጋፍ መልክ ማግኘቷን ዘግቧል፡፡ የተገኘው ገንዘብ በሒደት ላይ ላሉ እና ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል መሆኑን የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሐጂ ኢብሳ መግለጻቸውን ያሰፈረው ዘገባ የውጭ እርዳታና ድጋፉ የ2009 ዓ.ም በጀትን 18 በመቶ ይሸፍናል ማለታቸውን አስፍሮአል፡፡

ሀገሪቱ ከግብርና ከታክስ የበጀቷን 80 በመቶ ለመሸፈን መጠነ ሰፊ የሆነ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደምትገኝ የገለጸው ሺንዋ የኢትዮጵያ የኤክስፖርት ገቢ በታቀደው መልኩ አለመጓዙ በሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ረገድ ክፍተት መፍጠሩንም ገልጾአል፡፡

ዴይሊ ትረስት ድረገጽ በበኩሉ የኢትዮጵያ አየር መንገድ 59 ተጨማሪ አውሮፕላኖችን ሊገዛ መሆኑን ዘግቧል፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በመካከለኛ ጊዜ ውስጥ ለማሳካት ከነደፋቸው እቅዶቹ መካከል እ.ኤ.አ በ2025 አመታዊ ገቢውን በ2016/17 ከሚገኝበት 2.71 ቢሊዮን ዶላር ወደ 25 ቢሊዮን ዶላር ማሳደግ መሆኑን ገልጾአል፡፡

የደንበኞች እርካታ ሥራ አስኪያጅ ወይዘሪት ሰብለወንጌል አዘነ የአየር መንገዱን የረጅምና መካከለኛ ጊዜ የማስፋፊያ እቅዱን አስመልክተው በጽ/ቤቱ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እምንዳስታወቁት  አየር መንገዱ ከያዛቸው የማስፋፊያ እቅዶች ውስጥ አንዱ አሁን ያሉትን 92 አውሮፕላኖች በ2025 ወደ 151 ማድረስ መሆኑን በዚህም አየር መንገዱ ከ2017-2025 ድረስ ባሉት ስምንት ዓመታት ውስጥ ተጨማሪ 59 አዳዲስ አውሮፕላኖችን እንደሚገዛ መናገራቸውን ከዚህ ሌላም አየር መንገዱ በ2025፣ 22ሚሊዮን ደንበኞችን ለማጓጓዝ እንዲሁም የበረራ መዳረሻ ሀገሮችን ቁጥር ወደ120 ለማሳደግ አቅዷል፡፡

ሴቲ ደብሊው ኦንላይን ድረገጽ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለቦይንግ 767-300ERs አውሮፕላን በአዲስ መቀመጫዎችና በተለያየ የመዝናኛ ዘዴዎች ላይ የውስጥ እድሳት ማከናወኑን ዘግቧል፡፡ እድሳት የተደረገላቸው ስድስት ቦይንግ አውሮፕላኖች ለሕንድ ለመካከለኛው ምሥራቅና ለአፍሪካ መስመሮች አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው ታውቋል፡፡

ማሻሻያ የተደረገላቸው አውሮፕላኖች በውስጣቸው የመኝታ አገልግሎት፣ 17 ኢንች ፍላት ስክሪን ቴሌቪዥን፤ በጣም ዘመናዊ የሆኑ መብራቶች የተገጠመላቸው ሲሆን ለአውሮፕላኖቹ ማሻሻያ ለማድረግ ከስድስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ መደረጉን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ተወልደ ገ/ማርያም መግለጻቸውን ዘገባው ያስረዳል፡፡

በሌላ ዜና የቻይናው ዜና ወኪል ሺንዋ የኢትዮጵያ መንግሥት መጠነ ሰፊ የሆነ የፀረ-ሙስና እርምጃ በመውሰድ ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ 56 ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ ባለሀብቶች እና ደላሎች በቁጥጥር ሥር ማዋሉን በመግለጽ የፀረ-ሙስና ዘመቻው በ2008 ዓ.ም የተከሰተውን ሕዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ የመጣ የጥልቅ ተሐድሶው አጀንዳ አንዱ አካል መሆኑን የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ማስታወቁን ገልጾአል፡፡ መንግሥት ይህንን የመልካም አስተዳደር እጦት የሚፈጥረውን ችግር በጽኑ በመዋጋት ረገድ እየወሰደ ያለውን እርምጃ በሰፊው አጠናክሮ እንደሚቀጥል መግለጹን ሺንዋ አስፍሮአል፡፡

ሺንዋ በሌላ ዘገባው የኢትዮጵያ የወታደራዊ ሹሞችና የቻይና አቻዎቻቸው በወታደራዊ ዘርፍ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ነሐሴ 12 ቀን 2009 ዓ.ም በቤጂንግ የጋራ ምክክር ማድረጋቸውን ዘግቧል፡፡ የቻይና ምክትል የማእከላዊ የመከላከያ ኮሚሽን ፋን ቻንግሎንግና የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ጄኔራል ሳሞራ የኑስ በሁለቱ ሀገራት የመከላከያ ዘርፍ ላይ መወያየታቸውን፤ በቅርብ ዓመታት ቻይናና ኢትዮጵያ በፖለቲካውና በኢኮኖሚው ረገድ በጋራ መተማመን ላይ የመሠረቱት ግንኙነት ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ፋን ቻንግሎንግ መግለጻቸውን አስፍሮአል፡፡ ጀነራል ሳሞራ የኑስ በበኩላቸው የሁለትዮሽ ትስስራቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ መናገራቸው ተዘግቦአል፡፡ የኢትዮጵያ 7.9ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ከፍጹም ድሕነት የማውጣት እቅድ መያዟን የእርሻና ተፈጥሮ ኃብት ሚኒስትር ዳመነ ዳሮታ ማስታወቃቸውን፤ የተገባደደውን የ2009ዓ.ም በጀት ዓመት አቢይ የሥራ ክንውኖችን የገመገመው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በገጠር የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታ ለማሻሻል እቅድ መያዙን የሺንዋ ዘገባ ያስረዳል፡፡

ባለፉት ስድስት ወራት በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ የቻሉ 6.6 ሚሊዮን ዜጎችን በአየር ንብረት ጥበቃ፣ የመስኖ ልማትና በሌሎች የእርሻ እንቅስቃሴዎችም እንዲሳተፉ እድሉ እንደተመቻቸላቸው፤ ቁጥራቸው 1.3 ሚሊዮን የሚደርስ በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ ያልቻሉ የአካል ጉዳተኞችና አዛውንቶች ከመንግሥት ድጋፍ እየተደረገላቸው መሆኑን ሚኒስትሩ መናገራቸውን ዘገባው አመልክቶአል፡፡

ኳታር ድረገጽ በበኩሉ የኳታር የንግድ ምክር ቤት አባላት ነሐሴ 18/2017 ዓ.ም ከኢትዮጵያ የልኡካን ቡድን ጋር ተገናኝቶ በሁለቱ ሀገራት መካከል ስላለው የንግድ ግንኙነት እንዲሁም የንግድ ግንኙነቱን ማጎልበት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መወያየታቸውን ዘግቧል፡፡ ውይይቱ በእርሻ፣ ማእድን፣ በቤት ግንባታ እና በመሳሰሉት ዘርፎች ስላለው የኢንቨስትመንት እድል ትኩረት ማድረጉን በመግለጽ የኳታር-ኢትዮጵያ የንግድ ፎረም በሚዘጋጅበት ሁኔታ ላይ መወያየታቸውን አስታውቋል፡፡

የኳታር የንግድ ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚደንት መሐመድ ቢን አሕመድ ቢን ቶዋር አል ኩዋሪ ኢትዮጵያ ለኳታር ኢንቨስትመንት ተስፋ ሰጪ መሆኗን እንዲሁም የኳታር የንግድ ምክርቤት ባለኃብቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት እንዲሳተፉ የሚያበረታታ መሆኑን መናገራቸውንም ዘገባው ገልጾአል፡፡